# ጥሕሻ ምሁር ገብረሕይወት ባይከዳኝ እንክዘከር

======/////=====/////======/////======

ክቡራንን ክቡራትን፡ኣብ ጉዳይ ጥሕሻ ሙሁር ገብረሕይወት ባይከዳኝ ኣድሂበ ቅድሚ 3 ዓመት ሓደ ጽሑፍ ናብ ኣንበብቲ ኣቕሪበ ምንባረይ ትዝክሮ ትኾኑ ኢኹም እብል።ሕጂ ድማ ቅድሚ ሎሚ ኣብ ገጻት ማሕበራዊ መራኸቢ፡ ብቋንቋ ትግርኛን ኣማርኛን ኣድሂበ ዝሓናጠጥክዎ ይኹን ገለ ዉልቐ-ሰባት ዝጸሓፍዎ ኣብ ሓደ ኣካቲተ ኤቕርቦ ኣለኹ።

እቶም ዝመራመሩን መጽናዕታት ዘካይዱን ድማ ብዝበለፀ ከሰውድዎን ከጉላዕልዕዎን ተስፋይ ወሰን የብሉን።እሞ ሃየ ኢደይ ኢድኻ ንበል ክብል እፈቱ።ንክጽሕፍ ተታባብዑኒ ድማ ክብሪ ክህበኩም እረድይ።

“ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ብዛዕባ ሓደ ፀሓፊ ታሪኽ፡ከማልኦ ዘለዎ ነጥብታት ቢሎም ካብ ዝገለጽዎ ወሳንን ቐላስን ነጥብታት እዚኣን ይመስላ።

- ✓ ብመጀመርታ ንዝተገበሩ ፍጻሜታት ተዓዛቢ ልቦና ክህልዎ ኣለዎ።
- ✓ ካልኣይ ንዝተፈጸሙ ፍጻሜታት ፍርዲ ንምሃብ ዘየዳሉ ኣእምሮ ክውንን ኣለዎ።
- ✓ ሣልሳይ፡ንዝተዓዘቦን ንዝሃቦ ፍርድን ንምፍላጥ፡ንፁር ሣውያ ቋንቋ ክጥቀም ኣለዎ።

ኣብተን ሓጸርቲ ዕምሪ ሕይወቶም፡ክልተ መጽሓፍቲ ጽሒፎም ኢዮም።ንሳተን ድማ እዚኣተን ኢየን።

- ❖ "ኣጤ ምኒሊክና ኢትዮጵያ"፥
- ❖ "መንግስትና የሕዝብ አስተዳደር"



**እታ ንፈለማ ግዜ ዝተሓትመት፡መፅሓፍ ክቡርን ዓቢይን፡ሙሁር ገብረሕይወት ባይከዳኝ-እዚኣ እያ።**

ነጋድራስ ገብረሕይወት፡24 ሰነ 1911 ዓ/ም/ሓ፡ ካብዛ ዓለም ብሞት ተፈልዮም።እንተኹነ ገሊኦም ጸሓፍቲ ታሪኽን ተመራመርትን፡ኣብ መበል 31 ዓመቶም ኢዮም ሞይቶም ይብሉ።ገሊኦም ኣብ መበል 33 ዕድሚኦም ከም ዝሞቱ ይገልጹ ኢዮም።

"ሰብ ካብ ዓቢይ ይኩን ካብ ንእሽተይ ስድራቤት ይወለድ፡ርእሱ ንዓቢይ ስራሕ ከዳልው ኣለዎ።" ብዝብል ተጠቃሲ ሓሳብ እውን ይፍለጡን ይዝረኩን ኢዮም።”-11 ሓምለ 2018 ዓ/ም/ፈ

"ሰብ ካብ ዓቢይ ስድራቤት ይወለድ ካብ ንእሽተይ፡ንርእሱ ንዓቢይ ነገር ከዳሉ ኣለዎ።" ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ።

እዛ ጥቅሲ ጃንሆይ ደጋጊሞም ኤዘውትሩዋ ነበሩ።ብፍላይ ኣብ መባእታ ደረጃ ተመሃሮ ከለና፡ኣብ ጋዜጣ ሕብረት ደጋጊማ ትወጽእ ምብንባራ ካብ ግዜ ቁልዕነትይ ሚሒር ይፈትዋ ኢየ።

ብዛዕባ ነጋድራስ ገብረሕይወት ብዙሕ መጽናዕትን ምርምርን ኪግበር ነይርዎ ኢዩ።ዋላ እኳ፡ሕጂ ደሓን ኣፋፍኖት ተጀሚሩ ተሃለወ ግን ዳርጋ ኣይተሰርሐን ኢዩ።

ነጋድራስ ገብረሕይወት፡ኣብ ታሪኽ ዓለም ፍሉይ ቦታ ዘለዎ ምሁር ኢዩ።ኣብ ስነ ቁጠባ፡ኣብ ስነ ጽሑፍ፡ኣብ ምሕደራን ታሪኽን ጉሉሕ ኣስተዋጽኦ ኣለዎም ኢዩ።ኣብተን ተጻሒፈን ዘለዋ ጽሑፋቶም ብዙሕ፡ከሥብን ረብሓን ከም ዝተሓፍሰ ብዙሓት ሙሁራት ይምስክሩ ኢዮም።እንተኹነ ኣብ ገለ ገለ፡ነጥብታት ክእረም ዘለዎ ጉዳያት ኣለዉ፡ኢዮም።100 ዓመት ኣቁጺሩ ኣሎ፡መጽሓፎም ካብ ዝጽሕፍዎ።ኣብ 1910 ወይ ድማ 1918 ዓምፈ ታሪካዊት ዓመት ኢያ።”

“ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ከመይ እዩ ኣማውት'ኦም፧- 5 ነሓሰ 2016 ዓ/ም/ፈ

======//////=========///////==========///////=====

ብዛዕባ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ብዙሓት ሙሁራት፥ ኣብዚ ዝሓለፈ 100 ዓመት መበራብርን ኣንፈት ምርምርን መጽናዕትን ኮይንዎም እዩ።ነጋድራስ ገብረሕይወት ዘበርኸትዎ ደርማስ ኣስተዋጽኦ ኪንዮ ኣብ ኢትዮጵያ፣ ኣብ ዝተፈላለዩ ዩኒቨርስታት ንምርምርን መጽናዕትን ክኸውን ባብ ኣርሒዩ እዩ።

ኣጋጣሚ ኮይኑ፡ትማሊ ኣብ ጉዳይ ኣቶ ወልደ'ኣብ ወልደማሪያም 'ወልወል' ኣድሂብና ምስ ሓንቲ ተጋዳሊት ነበር ዕላል ከፊትና ህጁም ንብል።እታ ተጋዳሊት ፖለቲካዊ ትንታነ ክትህብ ከላ ደስ እያ ትብለኒ ወትሩ፣ሓደው ትሕትና ኣለዋ፡ብቲ ሓደው ኸኣ ልዝብ ኢላ ብምቕሉልል ኣገባብ እያ ትትንትን።

እዛ ተጋዳልቲ ነበር፡ዳርጋ መሰታ ኣደይ ትኽውን እያ።ግና ከም መሓዛይ እየ ዝርእያ ክብል ዝክእል።ክንዲ ዝኾነ ኸኣ፡ በቃ ደስ ዝበለና ጉዳይ  ኣልዒልና ብናጻን ብኩፉት ሳውያን መድረኽ ከፊትና፡ ኣብ መጋሪያ ዕላል እጃም እናበልና፣ንቕድሚት ንሳግም ኢና ኣብዝሓ ጊዜ።ኣብ ገለ'እዋን እውን ትርር ዝበለ መርገጽ ክሕዝ ከለኹ ከም ኣደ መጠን ምኽሪ ትምጥወኒ'ያ።

እሞ ደኣ ትማሊ፡ኣብ ጉዳይ ወልወል ኣድሂብና ክንዛራረብ ከለና፣ "ኣበይ ድዩ ትውልዶም፤ እዞም ኣብ ኤርትራ ብዕዙዝ ኣገባብ ፖለቲካ ስሞም ዝለዓል እንዲዩ ሓቀይ ትብለኒ፤"

ኣነ ኸኣ፡"እወ፡ ልኽዕ ኢኺ በልኽዋ።"

"እሞ ብዛዕብ'ኦም ብዙሕ እዩ ዝበሃል ግን ጥልቕ ዝበለ ኣፍልጦ የብለይን።" በለትኒ።

ኣነ ድማ፡ "እወ፣ንናጽነት ኤርትራ ተቓሊሶም እዮም፣ግና ትውልዶም ዋላ ባዕሎም 'ትግራዋይ እንዲኹም ምስ በልዎም፡ ኣብ ሓደ መድረኽ'፣ብዘይነግፈረግ ትግራዋይ ምኳኖም ከም-ዝገለጹ ብሰፊሑ ይንገር እዩ።ኣብ መጽሓፍ 'ኣይንፈላለ' ከማን ኣሎ እዩ።" ቢለ እምልሸላ።

ወሲኽ ኸኣ፡ "እወ ብዛዕባ ኣቦይ ወልደ'ኣብ ብዙሕ ይዝረብ እዩ።ወዲ ኣክሱም እዮም ዝብሉ ኣለዉ።ወዲ ተንቤን እዮም ዝብሉ ኤርትራውያን ኰነ ኢትዮጵያውያን ኣለዉ።ኮታ ብዙሕ ፍሉጥ ሰብ ተኮይንካ እትን እትን እዩ ዝበሃለልካ!" ኢለ ዘረባይ ቀጺለ…

"እምበር ዓዲ ኣዲኦም ኣብ ዓድዋ፡' ዞንጉይ'፣ዓዲ ኣብኦም ሽረ-እንዳባጉና'ዩ ዝበሃል ዓዶም"- በልክዋ ነዛ ተጋዳሊት ነበር መሓዛይ።

ንሳ ድማ፡"ብምግራም ዞንጉይ ደኣ ዓድና እንድዩ፣ ማለት ናይ ኣቦይ ኣብ ዞንጉይ እዩ፣ ናይ ኣደይ ኸኣ ኣብ ሎጎምቲ እዩ።ትፈልጦ ዲኻ፤" ትብለኒ።



ኣነ ድማ፡ "ናይ ታሪኽ ፈላጣትን ኣብ ሥነ-ዓውዲ ቑጠባ ሙሁራትን፣ዝኾኑ ኣብ ኣስመራ ብዛዕባ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ክዛረቡ ኸለዉ፣ብገለ ሸነኾም ወዲ ሎጎምቲ ምኳኖም ይዛረቡ ምንባሮም ቕጂል ይብለኒ እሞ፣ንነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ጓል ዓዶም ኢኺ፤ በሊ ክትሕግዝኒ ኢኺ ሓበሬታ ናቶም ስለ-ዘገድሰኒ፣ሃየ ንዓዲ ተኸይድኺ ወይ ተደዊልኺ ሓደራ ከይትርስዒ ኢኺ!" ክብላ ተቐሰብኹ።

"እዋእ፡፡ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ደኣ ነደይ ኣኩ'ኣ እንድዮም፣ይሕግዘካ እምበር ታሪኾም ተደሊኻዮ ደኣ፤" ትብለኒ።ብመሰረት ዕላልና ድማ ስም ወላዲት ኣዲኣ ወይዘሮ ጸሃይቱ ኪዳንኡ እዩ ዝበሃል በዓል ሎጎምቲ ድማ ኢየን።

ገሪሙኒ! ብሓጺር መንገዲ ፈጣሪ ከገባግበልኻ ኸሎ ይገርም ኢዩ፡ብዙሕ ግዜ ብከምዚ መንገዲ ኽንደይ ታሪኽ ይፈጥረለይ እዩ፣እሞ ብስራሕ ፈጣሪ ይገርመኒ'ዩ!
በሊ ሓደራኺ ኣብ ኣማውታን ግለ-ታሪኮምን ቀልዑት ኮይና ንሰምዖ ነገር ስለ-ዘሎ ኣጣልለለይ ኢኺ፤" በልኽዋ።

"ሕራይ! ከማን ኣማውት'ኦም፣'ብቕን'ኢ እዮም ተቀቲሎም እዩ' ተባሂሉ'ዩ ዝንገረና።" ምስ በለትኒ።
ኣመና ተገሪመ ምኽንያቱ፡ ኣብ ግዜ ኃይለሥላሴ ኾነ ኣብ ግዜ ደርጊ ብጸሓፍትን ብጋዜጠኛታትን ይኹን ሙሁራትን ኣማውታ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ፡ 'ብዝሓደሮም ሕዱር ሕማም፡ካብዛ ዓለም ብሞት ከምዘተፈለዩ' እዩ ዝዛረብን ዝጸሓፍን ነይሩ ዝብል ካብ ዝተፈላዩ ሙሁራትን ፈላጣትት ታሪኽ ደጋጊመ እሰምዕ ብምንባረይ፣ኣንክሮ ክወሃበሉ ዘለዎ ነጥቢ ምዃኑ ከስተውዕለሉ ሰፊሕ ኣፍደገ ፈጠረለይ።

ስለዚ፣ኣብዚ ጉዳይ ኣድሂብኩም ምርምርን መፅናዕትን ትገብሩ ሰባት፣ገለ ኣንፈት ይኾነኩም እዩ ዝብል ሓሳብ ኣለኒ።እቲ ምንታይ ታሪኽ ታሪኽ ስለ-ዝኾነ፣ይንዋሕ ይሕጸር ድማ እቲ ሓቂ ክዝረብን ክጸሓፍን ስለ-ዘለዎ ክእንፍተልኩም ይረድድ።
ብተወሳኺ፣ ኣብ 19 ክ/ዘመን፡ ኣብ ማይ-ኣባሻውል ብዙሓት ተጋሩ 'ኣብዝሓ ካብ ዓድዋን ኣክሱምን'፣ካብ ኣምሓራ 'ጎጃምን ጎንደርን' ካብ ደገ ከኣ ቱርካውያን ኣርመናውያን ካልኦትን ይነብሩ ብምንባሮም፣ንባጽዕ ወይ ንደገ ዝኸይድ ወድ-ሓበሻ ዘብ'ኡ፡ ኣብ ማይ ኣባሻውል ክዕርፍ ይቕሰብ ምንባሩ፣ብዙሓት ሰብ ዕድመ-ፀጋ ክዛረቡ እናሻዕ ይስማዕ እዩ።በዚ ድማ ነጋድራስ ኣብ ኣባሻውል የዕሪፎም ምንባሮም ዝዛረቡ ኣለዉ።



እቲ ስነ-ሞንትት'ውን ብመገዲ ኣስመራ ናብ ባጽዕ እቲ ተመራጻይ መገዲ ብምንባሩ በቲ መገዲ ምሕላፍ ንቡር እዩ ነይሩ።መሳለጥያ መጓዓዝያ ዝሓሸን ዝሰለጠን ተፈጢሩ ብምንባሩ ናብ እምኩሉ ይኹን ብኡኡ ኣቢሎም ናብቲ ዝበፅሕዎ መናገሻታት ክጓዓዙ ዕድል ኣርሒሎም'ዩ።

**ገብረሕይወት ባይከዳን ኣብ ጊዜ ቁልዕነቶም።**

በኒቶ ሞሶሎኒ፡ናብ ኮረሻ ስልጣን ምስ መጸ፣ብፍላይ ኣብ ፈለማ 1920ታት ፋሽስታዊነት ብዕሊ ምስ ተኣወጀ፣ኣብ ግዝኣት ጥልያን ዝኩና ዓድታት ድማ ተገልጸ፣ኣብ እንዳ-ማሪያም ኣብ'ዚ ከባቢ ዕዳጋ እንዳ ደርሁን ወዘተን ዝነበሩ ሓበሻ መብዛሕትኦም እቶም ኣብ ላዕሊ ዝተገጹን፣ እቶም ምስ ኣሉላ ኣባነጋ ከቲቶም ዝነብሩ ሰራዊት ኣብ ሓዳርን ኣብ ካልእ ሕይወትን ተጸሚድም ፋሕ ኢሎም ናብር'ኦም ይመርሑን ዝነብሩ ብምልኦም፣ካብቲ ፋሽስታውነት ዝተግሃደሉ ጊዜ ንደሓር፣ካብ ጆርጊያ ማይ ኣባሻውል ሰጊሮም ንላዕሊ ጥራይ ወድ ሓበሻ ክነብር ከምዝተወሰነ ዝምስኽሩን ዝገልጹን ብዙሓት እዮም።

እዚ ሕሳብ ንመራጎዲ ካብ ዝብል እዩ፣እምበር እቲ ፍረ-ነገሩ እንተስ በቲ እንተስ በቲ፣ነጋድራስ ገብረሕይወት ኣብ ወደብ ባጽዕ ምስ በጽሐ፣ከምቲ ኩልና ንፈልጦ ናብ ኤውሮጳ ናይ ምኻድ ዕድል ኣጋጥምዎም እዩ።

ከምቲ ገለ-ገለ ጸሓፍቲ ዝብልዎ ዘይኮነ ኸኣ፣ ኣብ ጀርመንን ኣብ ኦስትርያን እዮም ተማሂሮም እምበር ኣብ ኣውስትራሊያ ኣይኮነን።ሓማሴናዊ ሰብኣይ ብምእታወን እየን ወላዲቱ ሒዛቶ ከይዳ ዳኣምበር ምስ ብጾቱ ብምኺን ኣይኩነን ካብ ኣውራጃ ዓድዋ ናብ ምድረ-ሓማሴን ደሓር ናብ ባጽዕ ዝኸደ።

ይቕጽል…"

17 ጥቕምቲ 2020 ዓ/ም/ፈ ንመጽሔት ወይኒ ንሓፈሻዊ ኣንበብቲ ከም መኣረምታ ተሓሲቡ ዝተጻሕፈ ድማ እንህልኩም።ኣቐዲመ ግን ንስድራቤት ኣቦይ ኣጽብሃ ገ/ዉህበትን ንግራዝማች ጸጋይ ሓጎስን ኣብ ጊዜ ጥልያን ብቁልዕነቶም ዝሰምዕዎን ዝፈልጥዎን ምስክርነቶም ብምሃቦም ይኹን ኣሳእል ክወስድ ብምፍቃዶም ብዝለዓለ ብርኺ ከመሥግን እፈቱ።

"#ብዛዕባ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ኣድሂብኩም ኣብዚ ሰሙን ዝሓተትኹምኒ ብጹት ማሕበራዊ መራኸቢ፡ንገለ ነጥብታት ኣሕጽር ኣቢለ ክጠቕስ እፈቱ።

ኣብ ዝተፈላለዩ ጋዜጣታት፡ሬድዮን ተለቪዥን ጣብያን ይኹን ኣብ መጽሓፍቲ ይኹን መርበባት ሓበሬታትን ዝርከቡ፡ብፍላጥን ብዘይ ፍላጥን ጌጋ ሓበሬታ ተዘርጊሑ ኢዩ።ጌጋ ወይ ሓሶት ድማ መላሲ የብሉን ኢዩ፡ከምቲ "ሓንካስ ዘውረየ፡መላሲ የብሉን!" ዝበሃል ማለት ኢዩ።


ኣባሻውል!

ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ

"ንሓሶት ሽሕ ግዜ ተደጋጊምኻያ ድማ ሓቂ ትመስል!"- ዝብልዋ ኣለዉ ኢዮም።ኣረ-ገሊኦምሲ "ንሓሶት እልፊ ኣእላፍ ተደሂምካያ ሲ፡ሓቂ ኢያ ትኸውን!" ዝብሉ እውን ኣለዉ ኢዮም።

እሞ ኣብዛ መጽሔት ተዘርጊሑ ዘሎ ሓበሬታ ኣተኩርኩም ልቢ ሂብኩም እሞ ረኣይዎ ወይ ንበብዎ ኢኹም፣ክንደይ ዝእረም ነጥብታት ኣለዎ ኢዩ።

ብመሰረቱ ንስፊሕ መብርሂ ኣብ መርበብ ሓበሬታን ኣብ ገለ ማዕከናት ዜናን፡ቕድሚ ሎሚ ብሰፊሑ ገሊጸዮ ነይረ ኢየ፡ግን እናሻዕ እቲ ሓሶት ወይ ጌጋ ሓበሬታ ብምግውሑን ፅሑይን ጽፋፍን መጽናዕትን መርምርን ብዘይምኽያዱ፡ተሓጺብኻ ኣብ ጭቃ ኮይኑ ኣሎ።

እሞ ደኣ፡ሙሁር ስነ ቁጠባን ጸሓፍን ነጋድራስ ገብረሕይወት፡ናብ ኣስመራ ኣባሻውል ዝኸዱ፡ከምቲ ብርኽት ዝበሉ ጸሓፍቲ ዝብልዎ ዘይኮነሲ፡ወላዲት ኣዲኡ፡በዓል ቤተን ሽቃ ገብረሕይወት፡ኣብ ኩናት መተማ ብምስውኦም፡ምስ ሓደ ሓማሴናዊ ሰብኣይ ሓዳር ገይረን ኢየን፡ናብ ሕምብርቲ ከተማ ኣስመራ ዝኩነት ኣባሻውል ዝኸዳ፡ናይ ዚ ምስክር ኣቦይ ጸጋይ ሓጎስ፡ሸምጓሽ ሰብሓት ተስፋይን እዘን ኣብዚ ስእሊ ዘለዋ ሓላል ኣደ(ሎሚ'ቕነ ካብዛ ዓለም ብሞት ዝተፈለያ)ኣደይ ሕይወት ገብረሕይወትን ካብቶም ካብ ወለዶምን ኣብ ኣባሻውን ቕድሞ 80 ዓመት ዝሰምዕዎ፡ዛንታ ወለዶምን ደቂ ገዛውቶምን ኢዩ።



ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ኣብ ምዕባለ ስነ ቁጠባ ሃንዳስን ቀላስን ምኳኖም ምሁራት ሥነ ቁጠባን ተመራመርቲ ታሪኽን ዝገልጽዎ ሓቂ ኢዩ።ገብረሕይወት፡ኣብ እምኩሉ ከም ዝተምሃረ ኣይግለጽን ኢዩ።ናብ ባጽዕ ዝኸደሉ ኣገባብ እውን ካብቲ ክእረም ዘለዎ ነጥቢ ሓደ ኢዩ።



ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ካብ ጀርመን ምስ መጹ እውን፡ኣብ ኣባሻውል ይቕመጡ ነይሮም ኢዮም።ናብ ባጽዕ እውን እናሻዕ ይወርዱ ነበሩ።ብፍላይ ድማ ምስቶም ፈላሚ ናውቲ ማሕተም ካብ ኤውሮጳ ካብ ምኒሊክ ተላኢኾም ዘምጽኡ ዝነበሩ፡ወልቀታይ ብጻዮምን ምስ ማህደረ ቃል ተወልደመድህን ይኹን ምስ ክቡር ኣቶ ጳውሎስ መንኣመኖም(ናይ ማሕርሮ ብጻዮም) ብምኳን ይመላለሱ ነይሮም ኢዮም።

→ <u>**ብላታ ኣጽብሃ ምስ ኣበምነት**</u>

ኢኖ ሊትማን፡ካብ ከረን ናብ ዓድዋን ኣክሱምን ከመጽእ ከሎ፡ምስቶም ዓቢይ ምሁር ኣዝማች ገብረሚካኤል ግርሙ(ኣከለጉዘታይ)፡ኣብ ታሪኽን ቋንቋን ኣብ ዘድንዓሉ እዋን ብኣላይለነት ደጃዝማች ገብረሥላሴ፡ምስ ካህናት ካቶሊክን ኦርቶደክስን ክላዘቡን ኢሂን ምሂን ክበሃሃሉን ኸለዉ፡ብጉድለት ጥዕና ምኽንያት ከም ትጽቢቶም ከሳትፍዎ ኣይከኣሉን ኢዮም።ግን እጃሙ ብተዘዋዋሪ እገብር ነይሩ ኢዩ።

ብሓጺሩ ኣብ ጉዳይ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ማማ ሕይወት ገብረሕይወትን በዓል ቤተን ብላታ ኣጽብሓ ገብረሕይወት፡ብጽሑፍ ሰናዶሞ ተሃልዮም፡ምስ ወዶም ክቡር ፓስተር ታደሰ ተዘራሪብና፡ገለ ክንገብር ተሰፋ እገብር።ወደሓንኹም!"

"#ሒስ

ኢትዮጵያ ውስጥ ካላደጉ የኪነት ዘርፎች አንዱና ዋነኛው-ሒስ ነው።የተጋነነ ነቀፌታ ወይም እጅግ የበዛ ሙገሳ የበዛበት አካሄድ እንጂ ሞያዊ የሆነ የተመዛዘነ ሒሳዊ ሥራ የሚሠሩም ሆነ የሚያሠሩ የኪነት ሰዎችና ጸሓፍያን እጅግ ኅዳጣን ናቸው።

በአለም ደረጃ የሒስ ሞያ በጥንታዊው የግሪክ ሥልጣኔ ከነ አሪስቶትል ጊዜ የጀመረ ነው።ባደጉት ሃገራት የሒስ ሞያ የዳበረ በመሆኑ ጥልቀት ያላቸው የኪነት ሥራዎች እንዲወጡ፣የሃገራቸውና የቋንቋቸው ጥበብ እንዲያድግ የላቀ ሚና ተጫውቷል።

የኪነት ሥራ ዘመንን የሚነግር፣ሥራው በተሠራበት ጊዜ የነበረ ማኅበራዊ ሁነት ስሎ የሚያሳይ፣ትውልድን በመልካም ስብእና የሚገነባ፣ዕውቀትን የሚያስጨብጥ...በመሆኑ የጠራ መንገድ የሚያሳይ ግድፈትን የሚከላከል በደራሲ (ወይም ከያኒ) እና በተደራሲ መሃል ሆኖ የሚያገናኝ የሂስ ባለ ሞያ እጅግ አስፈላጊ ነው።

የሒስ ባለ ሞያ ከያኒውን (ጸሓፊው) ሳይሆን ኪነቱን (ድርሰቱን) መሠረት በማድረግ የሥራው ዓላባውያን፣መኀበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እይታን መሰረት አድርጎ ዘመኑን ያልለቀቀ እይታ የሚያስፈልገው ነው።ሒስ ከውግንና፣ፍርሓትና ጥቅም ጋር ፈጽሞ መገናኘት የሌለበት ሞያም ነው።

ዘመናዊው ኢትዮጵያ ውስጥ ሒስ ሲነሳ ቀድሞ የሚነሳው ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ ነው። ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ የመጀመርያው ሰው እንደሆነ ይታወቃል።



- መረጃዎችን አስደግፎ ሚዛናዊ ሒስ ማቅረቡ
- ጸሓፊውን ሳይሆን ጽሑፉን ብቻ ለይቶ ማሔሱ
- ጸሓፊውና ንጉሠ ነገሥቱ በህይወትና በሥልጣን ላይ እያሉ በድፍረት መጽሔት ላይ እንዲታተም በማድረጉ

በ1900ዎቹ ገብረህይወት የሂስን አጻጻፍ አሳይቶ የነበረ ቢሆንም እስከ አለንበት ዘመን የሒስ ሞያ በሚገባ እየተሠራበት አይደለም።

ሐያሲያን ብለን የምንጠራቸው ውሱን ሰዎች ቢኖሩም፣በሁሉም ተደራሲ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ጎምቱ ሓያሲ አለ ለማለት ግን አስቸጋሪ ነው።እርግጥ ነው የሒስ ሞያ ስር እንዲሰድና ተቀባይነት ኖሮት እንዲጎመራ ሌት ተቀን የሚጥሩ የኪነት ሰዎች እንዳሉ መካድ አይቻልም።ገብረህይወት እንዳደረገው ሳያጎበድድ፣መሪዎችን ሳይፈራ፣በሁኔታዎች ላይ "ደገፍ" ያላለ ፊት ለፊት የሚራመድ ደፋር ሓያሲ ግን የለንም ብሎ መናገር ይቻላል።" በጋዜጠኛ ዮሃና ተለጥፎ መጠነኛ ማስተካከያ የተደረገበት ጽሑፍ ነው።

“ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡የብዙኃን አርአያ የሆኑት ምሁር ናቸው።ደራሲ፣ሐኪምና የምጣኔ-ሐብት ጥናት ባለ-ሙያ የነበሩት ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ የተወለዱት ከዛሬ 135 ዓመታት በፊት (ሐምሌ 24 ቀን 1878 ዓ/ም) ነበር።




ነጋድራስ ገ/ሕይወት የተወለዱት በታሪካዊቷ ዓድዋ አውራጃ ልዩ ስሙ ዞንጉይ በተባለ መንደር ነው። የኢትዮጵያ ወደ ኋላ መቅረት አሳስቧቸው ከእድሜያቸው በላይ የደከሙ ምሁር ናቸው።ምዕራባውያን ከጊዜ በኋላ ተግብረዋቸው ታዋቂና ገናና የሆኑባቸውን የምጣኔ-ሀብት አውድ (Economics) ጽንሰ-ሓሳቦች ነጋድራስ ገብረሕይወት ከብዙ ዓመታት በፊት ቀድመው ያውቋቸው እንደ ነበር በርካታ ምሁራን ይናገራሉ።በጥናትም ተረጋግጦዋል።

ከዚህ በተጨማሪም፣የነጋድራስ ገብረሕይወት ሃሳቦች የረቀቁና የመጠቁ በመሆናቸው ለብዙ ምርምሮችና የፖሊሲ ሃሳቦች ግንባር ቀደም ግብዓት እንደነበሩና ገና አሁንም እንደሚሆኑም የተለያዩ ታዋቂ ተመራማሪዎችና ምሁራኑ ይስማማሉ።

የነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝን የምጣኔ-ሐብት ጽንሰ-ሐሳቦች አዋቂነት ደጋግመው ከሚናገሩት ግለ-ሰቦች መካከል አንዱ የሆኑት የምጣኔ-ሐብት ጥናት ባለ-ሙያው ፕሮፌሰር አለማየሁ ገዳ፣‹‹ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በምጣኔ-ሐብት ዘርፍ፣በተለይም በልማታዊ ምጣኔ-ሀብት (Development Economics) መስክ በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት የዓለማችን ምሁራን መካከል አንዱ ናቸው›› ብለው ያስተምራሉ፤ይከራከሉ።

“ አእምሮ የሌለው ሕዝብ ሥራት የለውም። ሥራትም የሌለው ሕዝብ የደለደለ ኃይል የለውም። የኃይል ምንጭ ሥራት ነው እንጂ የሠራዊት ብዛት አይደለም። ሥራት ከሌለው ሰፊ መንግሥት ይልቅ በሕግ የምትኖር ትንሽ ከተማ ሞያ ትሠራለች። … ”
-ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ( “አጤ ምኒልክና ኢትዮድያ”፣ ገፅ-10)

”አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ” እና “መንግሥትና ሕዝብ አስተዳደር” በተሰኙት መጽሐፎቻቸው እንኳን ያን ጊዜ ዛሬም ከምሁራኖቻችን በማንጠብቀው ደግነትና የጠለቀ ብስለት የተሞላበት ትንተናና በቀላል ቋንቋ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው የሚመኙትን የእድገት ሐሳቦችን ያሰፈሩ ቁንጮ ምሁር ናቸው።

“መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር” የተባለውና “State and Economy of Early 20th Century Ethiopia” ተብሎ ወደ እንግሊዝኛና ተተርጉሞ የታተመው መጽሐፋቸው፣ለብዙ ችግሮች መፍትሄ የሚሆኑና እጅግ የበዛ ፋይዳ ያላቸውን የምጣኔ ሀብት ጽንሰ ሐሳቦችን ያካተተ መጽሐፍ መሆኑን ይታወቃል።

ነጋድራስ ገብረሕይወት ወደ ጀርመንና ኦስትርያ በመሄድ የሕክምና ትምህርት አጥንተዋል። በአፄ ምኒልክ ቤተ-መንግሥትም ፀሐፊ በመሆን ሠርተዋል።የድሬዳዋ ጉምሩክ ኃላፊም ሆነው ተመድበው አገልግለዋል።ደግ የማይበረክትላት ኢትዮጵያ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝን በሞት የተነጠቀችው ገና በጎልማሳነት እድሜያቸው የመጀመሪያ ዓመታት ነበር።

ሥለ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ወደ-ፊት ብዙ የምንወያየውና የምንጽፈው ነገር ይኖረናል!”

“ነጋድራስ ገብረሕይወት በ1878 ዓ/ም በአድዋ አውራጃ ተወለዱ።በልጅነታቸው ወደ አሥመራ በማምራት፥ከዛም ወደ ምፅዋ አጠገብ እምኩሉ በሚገኘው የስዊድን ሚሲዮን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ቀሰሙ።ከዚያም ወደ ኦስትርያ በመርከብ ተደብቀው ከሄዱ በኋላ የህክምና ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። እንዲሁም የውጪው አለም የፖለቲካ፣ኢኮኖሚና ማህበራዊ መስተጋብሮችን ቀስመው ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ችለዋል።

ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ አፄ ምኒልክ በጠና የታመሙበት ጊዜ በመሆኑ አፄ ምኒልክን፡ለማከም ከተሰባሰበው የህክምና ባለሙያ መካከልም አንዱ ነበሩ።

ገብረሕይወት ባይከዳኝ አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ እንዲሁም መንግስትና የህዝብ አስተዳደር የተሰኘ አጭር ግን እምቅ ሐሳብ የያዘ መፅሀፍትንም አሳትመዋል።ይሄ መፅሀፍ ኢትዮጵያን በልማት ጎዳና ወደ ፊት ለመውሰድ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ግልፅና ቀጥተኛ በሆነ ቋንቋ ያሰፈሩት ነው።

ገብረሕይወት ባይከዳኝ የህይወታቸውን በፖለቲካ፣በኢኮኖሚና በማህበራዊ ምርምር ብቻ ሳይገድቡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሀገራቸው ብዙ ስራዎችን ሰርተዋል።መጀመሪያ በምድር-ባቡር በተቆጣታሪነት ደረጃ ካገለገሉ በኋላ እስካሁን በትምህርት ዘርፉ ካገኙት ማእርግ ይልቅ፡በሚታወቁበትን ማዕረግ ባገኙበት የነጋድራስነት በድሬዳዋ ሰርተዋል።ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆዩ በተወለዱ በ33 ዓመታቸው በ1911 ዓ/ም አማሟሟታቸው በውል ሳይጠናና ሳይታወቅ ሕይወታቸው ተቀጥፈዋል።"

# "ኢትዮጵያ ለምን ኋላ ቀረች?"-በ*ግርማ ሞገስ እንደተጻፈ*

"ኢትዮጵያ ከውጭ ወረራ ረጅም የነፃነት ዘመን እንዳላት የሀገር ተወላጅ እና የውጭ ሀገር የታሪክ ተመራማሪዎች ያረጋግጣሉ።

ይሁን እንጂ በሥልጣኔ ግን ብዙም እንዳልገፋች ይኸው ዛሬ የእኛም ትውልድ ሳይቀር የሚያየው ሐቅ ነው።

ይኽ እንዴት ሊሆን ቻለ? ረጅሙን የነፃነት ዘመን በሥልጣኔ ወደፊት ለመራመድ ለምን አልተጠቀመችበትም ኢትዮጵያ? ምን ስትሠራ ነበር? የሚሉት የቁጭት ጥያቄዎች የሁላችንም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጥያቄዎች ናቸው።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን በራሳቸው አነሳሽነት አውሮፓውያን ጎብኚዎችን እና ሚሲዮናውያንን እየተከተሉ ከሀገራቸው ወጥተው የፖለቲካ ሳይንስ፣የሕክምና፣የምህንድስና፣የኢኮኖሚ፣የመንገድ ሥራ የመሳሰሉ ዘመናዊ (Secular) ትምህርት ቀስመው ሀገራቸውን ለመርዳት ወደ ሀገራቸው የተመለሱት የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ምሁራን የእነ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ (1886-1919) ሁሉ የቁጭት ጥያቄ ነበር።

በጣት የሚቆጠረው የነገብረሕይወት ትውልድ የውጭ ትምህርት ቀስሞ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰው ባዬ ምኒልክ ዘመን ነበር። ይሁን እንጂ ለዘመናዊነት በር የተከፈተው ባዬ ኃይለሥላሴ ዘመን እንደነበር፣ በኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ1942 ዓመተ ምህረት (እ.ኤ.አ. 1950) የአዲስ አበባ የተፈጥሮ እና የሶሻል ሣይንስ ኮሌጅ መከፈቱን፤ኮሌጁ የተደራጀው በኢትዮጵያ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመክፈት በንቃት ይሠሩ በነበሩ ካናዳውያን እየሱሳውያን (Jesuits) ሲሆን፣የተማሪዎቹ ቁጥር ከ100 በታች እንደነበር ክፍሉ ታደሰ (The Generation, p.15-16) ያመለክታል።እሱም ቢሆን እጅግ ዘግይቶ የመጣ በውቅያኖስ ላይ ያረፈ ትንሽ ጠብታ ያህል ነበር።..."

**ኣብ መወዳእትታ ድማ ክቡር ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ንታሪኽ ዘመዛብዑን ብክሕደት ሃገር ኣሕሚሞም ዝውቐሱን ነጋድራስ ኣፈወርቒ ገብረየሱስ ብትሪ ይጽሕፍሎምን ሂስ ይህብሎም ምንባሮም ታሪኽ ሕርሕራይ ገይሩ ይሕበረና ኢዩ፥ዋላ እኳ ብወገነይ ወገንኻን ብሻራነትን እቲ ሓቂ ብብ ዝጽሕፉ ዝደፍኑን ዝቐብሩን ተበዝሐ ማለት ኢዩ።ብዝኰነ ኩቡራት ኣንበብቲ እዛ ስዒባ ዘላ ጽሕፍቲ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውደ ዝጸሓፍዋ ብመጠኑ ሚዛናዊት ተመሰለት ግን ነጋድራስ ኣፈወርቒ ግቡእን ቅርዑይን ስእሎም ተርእይ ብዘይምኳና ሓደ ምዕልቲ ነዛ ጽሕፍቲ ናብ ትግርኛ ተርጕመን ኣብ ኣስመራ ኮይኖም ዝገብርዎ ዝነበሩን ዉዳሴ ከንቱ ዝኾነ ጽሕፎም ኣሰንየ ከቕርቦ ክፍትን ኢየ።ክብሪ ግን ነቶም ንስለ ሓቅን ፍትሕን ብድፍረት ገጽ ንጉሥ ከይረኣዩን ከይፈርሑን ታሪኻዊ ጽሑፋት ዝጸሓፉ፡ተባዕ ሙሁር ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ክብል እደፍር'የ።**

**"ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ (1860-1940) በፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ አይን፣**
**(ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በእንግሊዝኛ እንደጻፉት፣ ሲሣይ ተፈራ ወደ አማርኛ እንደተረጎመው)**

**- ነጋድራስ አፈወርቅ በ20ኛው ክ/ዘመን መጀመርያ በሥነ-ጽሁፍና በስነ-ጥበብ ዘርፍ ከሚታወቁ ፋና ወጊ ጥቂት ኢትዮጵያዊያን መካከል አንዱ ናቸው፣**

**- ነጋድራስ አፈወርቅ ከኢጣሊያ ጋር በአድዋና በማይጨው በተደረጉት 2 ታላላቅ ጦርነቶች አገራቸውን በመክዳት በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን የሚወቀሱ ሰውም ናቸው፣ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ በደቡባዊ የጣና ሐይቅ ደሴት ክፍል በምትገኘው ዘጌ በሐምሌ ወር 1860 ዓ.ም ተወለዱ። በታዋቂው አያታቸው በመምህር ድንቄ ጠባቂነት በአካባቢው በምትገኘው ኡራ ኪዳነምህረት ቤተ-ክርስትያን የተለያዩ ሀይማኖታዊ ትምህርቶችን እየተከታተሉና ጎን-ለጎንም በአካባቢው በሰፋት በሚዘወተረው የባህላዊ ስእል ስራ ላይ እየተሳተፉ አደጉ።**



**ከ1872 ዓ.ም በኋላ በእቴጌ ጣይቱ አማካኝነት አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ ከዳግማዊ ምኒልክ ጋር እንዲተዋወቁ ተደረገ። በዚህ ጊዜም አፈወርቅ የኢጣሊያ መልእክተኛ ከሆኑት ከካውንት ፔትሮ አንቶሎኒ ጋር የመተዋወቅ እድል አገኙ። መልእክተኛው አንቶኖሊም በአፈወርቅ የስነ ጥበብ ዝንባሌ በመደነቅ አፈወርቅን ወደ ኢጣሊያ ወስደው ለማስተማር ለዳግማዊ ምኒልክ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ይኸው ተፈቀደላቸው።**

በመስከረም ወር 1880 ዓ.ም አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ የመጀመሪያቸው የሆነውን ጉዞ ወደ ኢጣሊያ አደረጉ። በኢጣሊያ ሲደርሱ የተደረገላቸው አቀባበልም ለዲፕሎማቲክ መልእክተኛ የሚደረገውን አቀባበል ይመስል ነበር። አፈወርቅ ከኢጣሊያው ንጉሥ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ ጋር በመገናኘት ከዳግማዊ ምኒልክ የተላከውን ስጦታ ለኢጣሊያው ንጉሥ አስረክበዋል። አፈወርቅ በኢጣሊያ ከደረሱ በኋላ በቱሪን በሚገኘው አለምአቀፍ ኢንስቲትዩት የአልበርቲና የስነ-ጥበብ አካዳሚ ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ ተደረገ።

በራስ መኮንን የሚመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በ1881ዓ/ም ኢጣሊያን በጎበኝበት ወቅትም አፈወርቅ ከማይታወቅ አንድ የሥነ-ጥበብ ተማሪነት ደረጃ የልዑካኑ ህጋዊ አስተርጓሚ ለመሆን በቁ።ራስ መኮንን ወደ ኢጣሊያ የተጓዙት የውጫሌ ውል ከተፈረመ በኋላ ሲሆን ኢጣሊያ ከደረሱ በኋላም ባለማወቅ ከመረብ ምላሽ ያለውን ግዛት ለኢጣሊያ የሚሰጥ ሌላ ስምምነት በኔፕልስ ፈርመዋል።አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ በውጫሌ ውል የአማርኛና ጣሊያንኛ ቅጂዎች መካከል ያለውን ልዩነት በመጀመሪያ በማወቅ ለራስ መኮንን የነገሩት እሳቸው መሆናቸውን በኋላ ቢናገሩም፣በእሳቸው አስተርጓሚነት በኔፕልስ በድጋሚ የተፈረመውን በተንኮል የተሞላ ሌላ ስምምነት ግን ለማስቀረት አልቻሉም።

አፈወርቅ ገብረኢየሱስ በራስ መኮንን ከተመራው የልዑካን ቡድን ጋር በሐምሌ ወር 1882 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል። የተመለሱበት ጊዜም በውጫሌ ውል አንቀጽ 17 የአማርኛና ጣሊያንኛ ቅጅዎች መካከል ያለው ልዩነት በግልጽ የታወቀበት ጊዜ ነበር።አፈወርቅ በኢትዮጵያ የኢጣሊያ መልእክተኛ ለነበሩት ሊዮፖልዶ ትራቨርሲ በአስተርጓሚነት ማገልገላቸው በማያወላዱት የጸረ-ኢጣሊያ እንቅስቃሴ መሪ በእቴጌ ጣይቱ ተወዳጅነትን አላተረፈላቸውም።

በእቴጌ ጣይቱና በአፈወርቅ መካከል ስለነበረው አለመግባባት ሌሎች ምክንያቶችም አዘውትረው ይጠቀሳሉ። አፈወርቅ ወደ እንጦጦ ራጉኤል ቤተ-ክርስትያን ጫማቸውን ሳያወልቁ በመግባታቸውና አግባብነት የሌለውን የእቴጌን ስእል በመሳላቸው በሁለቱ መካከል አለመግባባት መከሰቱን በመግለጽ አንዳንድ ምንጮች ጽፈዋል። ሌሎች ምንጮች ደግሞ ስእሉ ከነአካቴው በአፈወርቅ ያልተሳለና በኢጣሊያ መንግስት በስጦታ የተላከ መሆኑን በመግለጽ በሁለቱ መካከል ለነበረው አለመግባባት ሽፋን ከመሆን ውጭ እውነተኛ ምክንያት አለመሆኑን በመግለጽ ይከራከራሉ።

ለማንኛውም አፈወርቅ ከእቴጌ ንዴት ለጊዜው የሚያመልጡበትን እድል አገኙ።በኢጣሊያ ወዳጅነት በእቴጌ የተጠረጠሩትን አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ፣ የዳግማዊ ምኒልክ አጎትና አማካሪ የሆኑት የራስ ዳርጌ ልጅ ልጅ ጉግሳ ዳርጌና የአዛዥ ዛማኤል ልጅ የሆኑት ልጅ ቀጣው ዛማኤልን ከእቴጌ ቁጣ በተቻለ መጠን ለማራቅ በመስከረም ወር 1887 ዓ/ም በዳግማዊ ምኒልክ ትእዛዝ በአማካሪያቸው በኢንጂነር አልፍሬድ ኤሊግ አማካኝነት ወደ ስዊዘርላንድ ኒዩካተል/ኒዩቻተል ወደ ሚገኘው አለምአቀፍ ኮሌጅ ለትምህርት በሚል እንዲሄዱ ተደረገ።



አፈወርቅ ከአልፍሬድ ኤሊግ ጋር የቅርብ ጓደኛ የነበሩ ሲሆን አልፍሬድ ከኢትዮጵያዊት ሚስታቸው የወለዱትን ልጅም አግብተዋል።የእቴጌን ንዴት ለማብረድ በሚል አፈወርቅ ከስዊዘርላንድ የክርስቶስትን ስቅለት የሚያሳይ ምስል ወደ ኢትዮጵያ ለእቴጌ ቢልኩላቸውም፣ እቴጌ "ይስቀልህ! ይስቀልህ! ስቅል ያድርግህ!" May the Lord crucify you a hundred times! የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው እራሳቸው አፈወርቅ ጽፈዋል።

አፈወርቅ በስዊዘርላንድ ሳሉ ከአድዋ ጦርነት 2 ወር በፊት በእናት አገራቸው ላይ የመጀመሪያውን የክህደት ተግባር ፈጸሙ።አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ፣ ልጅ ጉግሳ ዳርጌና ልጅ ቀጣው ዛማኤል በታህሳስ ወር 1888 ዓ/ም የስዊዝ-ኢጣሊያን ድንበርን አቋርጠው ወደ ኢጣሊያ በመግባት የኢጣሊያን መንግስት ማገልገል ጀመሩ።

ይህ የክህደት ተግባር ለፍሬ የበቃውም አፈወርቅ ከኢጣሊያው ወዳጃቸው ከትራቨርሲ ጋር ባደረጓቸው ግንኙነቶች ምክንያት እንደሆነ ይታመናል።አፈወርቅ በጎጃም ያላቸው ንብረት ምናልባትም በእቴጌ ትዕዛዝ የመወረሱ ዜና መስማቱ አፈወርቅንና አብረዋቸው ለት/ት ወደ ስዊዘርላንድ የተጓዙትን 2 ልጆች ኢጣሊያን እንዲያገለግሉ ገፋፍቷቸው ሊሆንም ይችላል።በኢትዮጵያ በኩል ስላለው አጠቃላይ ሁኔታ ታማኝ መረጃ ባለማግኘታቸው ምክንያት 3ቱ ወጣቶች የኢጣሊያ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ሆነው ሊሆን እንደሚችልም ይገመታል።

የክህደቱ ምክንያት ምንም ይሁን ኢጣሊያ ጊዜ ሳታጠፋ አፈወርቅንና ከሳቸው ጋር ያገኘቻቸውን 2 ውድ አገልጋዮች ከኢጣሊያ ወደ ምጽዋ ላከቻቸው።3ቱ ወጣቶች በታህሳስ ወር መጨረሻ 1888 ዓ.ም ምጽዋ የደረሱ ሲሆን በጥር ወር 1888 ዓ.ም አጋማሽ ደግሞ በኤርትራ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ከሆኑት ጄኔራል ባራቴሪ ጋር ዕዳጋ ሓሙስ በሚገኘው ዋና ማዘዣ እንዲገናኙ ተደረገ። የኢጣሊያ ዋና አላማ ከ3ቱ ወጣቶች መካከል የሸዋ ንጉሥ የነበሩት የሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ የሆነውን ልጅ ጉግሳ ዳርጌ በዳግማዊ ምኒልክ ላይ የዘውድ ይገባኛል ጥያቄ እንዲያቀርብ በማድረግ ኢትዮጵያውያንን ለመከፋፈል የነበረ ቢሆንም እቅዱ ወደ ተግባር ሳይለወጥ ኢጣሊያ በአድዋ ሽንፈት በመቅመስዋ ወጣቶቹ ወደ አስመራ እንዲመለሱ ተደረገ።

ይህንን ተከትሎም አፈወርቅ ወደ ኢጣሊያ በመመለስ በህይወታቸው መሰረታዊ የሚባሉ ተግባሮችን አከናውነዋል። በቱሪን ለአጭር ጊዜ በመቆየት ወደ ኔፕልስ በመጓዝ ከታዋቂው የኢትዮጵያ ወዳጅ ፍራንሲስኮ ጋሊና ጋር በአለም-አቀፉ የኦሬይንታል ኢንስቲትዩት መስራት ጀመሩ። በ1896 ዓ.ም አፈወርቅ በቱሪን የተዋወቋትን ኡጌኒያ ሮዚን አገቡ።በኔፕልስ በቆዩባቸው ከ1896 ዓ/ም እስከ 1904 ዓ/ም ድረስ ባሉት ጊዜያትም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን ጦቢያ የተሰኘውን የልቦ-ወለድና ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የተሰኘውን የታሪክ መጽሀፍት አዘጋጁ። የኢጣሊያ-አማርኛ የንግግር ዘይቤና የተጓዦች መመሪያ የተሰኙት ጽሁፎችን አፈወርቅ ያዘጋጁትም በዚህ ጊዜ ነበር።

በ1904 ዓ/ም አፈወርቅ በኤርትራ የኢምፖርት-ኤክስፖርት ድርጅት በማቋቋም ወደ አገራቸው ኢትዮጵያ ተጠጉ።የዳግማዊ ምኒልክ ሞትና የወጣቱ የልጅ ኢያሱ የምኒልክ አልጋ ወራሽ መሆን አፈወርቅ ኑሮን በአዲስ መልክ በኢትዮጵያ እንዲጀምሩ ተስፋ ስለሰጣቸው ልጅ ኢያሱን የሚያሞግሱ ግጥሞችንም መጻፍ ጀመሩ።

ይሁን እንጂ ልጅ ኢያሱ አለመታደል ሆኖ በአገር ውስጥና በውጭ ጠላቶቻቸው ትብብር በ1908 ዓ/ም ከስልጣን በመወገዳቸው የስልጣን ጊዜያቸው አጭር ሆነ። በቀልጣፋ ስብእናቸው የሚታወቁት አፈወርቅም ጊዜ ሳያጠፉ ልጅ ኢያሱን ባሞገሱበት ብእራቸው አወገዟቸው።ይህም በአዲስ አበባ የተሰየሙትን አዲሶቹን ባለስልጣኖች አስደሰተ።

በመጨረሻም አፈወርቅ ተሳክቶላቸው በ1909 ወይም በ1910 ዓ/ም በራስ ተፈሪ መኮንን ግብዣ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ገቡ። በመጀመሪያ ሹመታቸውም በዩናይትድ ስቴትስ የኢትዮጵያ የንግድ ልዑክ ሆነው እንዲያገለግሉ ተደረገ። ከዚህ በመቀጠልም የምስራቅ ኢትዮጵያዋ ጠቃሚ የንግድ ከተማ የሆነችው የድሬደዋ ነጋድራስ ሆነው የተሾሙ ሲሆን ከ1917 ዓ/ም እስከ 1922 ዓ/ም ድረስ ደግሞ በውጭ አገር ሰዎችና በኢትዮጵያውያን መካከል ያሉ ክርክሮችን እንዲዳኝ የተቋቋመው ልዩ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ሆነው በመሾም በከፍተኛ ታታሪነት አገልግለዋል።

አፈወርቅ በ1910ዎቹ መጨረሻ /በ1920ዎቹ መጀመሪያ በብርሃንና ሰላም ጠንካራ ትችቶችን ከሚያወጡ ጥቂት ጸሀፊዎች መካከል አንዱ ነበሩ። በዚህ ጊዜም ፍትሃ-ነገሥትንና ይህንንም መሰረት በማድረግ ለበርካታ ክ/ዘመናት የግብጽ ቤተ ክርስትያን ለኢትዮጵያ ጳጳሳትን የመሾምዋን ጉዳይ በሰላ ብእራቸው አጥብቀው በመተቸት በአንድ ጽሁፋቸው "የእስክንድርያ ካህናት ብቻ ጥዋትና ማታ ከእግዚአብሔር ጋር ቆይታ ያደርጋሉን? ለነሱ ብቻ ከሥላሴ ጋር የሚነጋገሩበት የተለየ በውቅ የተሰራ ስልክ አላቸውን?" ብለው ጠይቀዋል። ይህም በሂደት ፍሬ አፍርቶ በ1921 ዓ/ም አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በአሌክሳንደርያ እንዲሾሙ እንዲሁም በ1951 ዓ/ም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያሪክ እንዲሾሙ መሰረት ሆኗል።

አፈወርቅ በኢጣሊያ ጉዳይ ያላቸውን የላቀ እውቀት መሰረት በማድረግ በ1925 ዓ/ም በኢጣሊያ የኢትዮጵያ ጉዳይ ፈጻሚ ሆነው ተሾሙ።ይሁን እንጂ የ2ኛው የኢጣሊያና ኢትዮጵያ ጦርነት ከመጀመሩ ጥቂት አመት በፊት በኢጣሊያ ወዳጅነት የሚታሙትን አፈወርቅ በኢጣሊያ ጉዳይ ፈጻሚ አድርጎ መሾም ለኢትዮጵያ ራሷን በራሷ የመግደል ያህል እንደነበር በመግለጽ አንዳንድ ጸሀፊዎች ይተቻሉ።

አፈወርቅ በሮም የኢትዮጵያ ጉዳይ ፈጻሚ ሆነው ስራቸውን የጀመሩት በችግር ነው። በበጀት ችግር ምክንያት ሚስጥራዊ የቴሌግራም መልእክቶችን ጭምር በኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በኩል ይልኩ ነበር። የሚልኳቸው መልእክቶችም አንዳንዴ እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ነበሩ።

የኢጣሊያ የቅኝ ግዛቶች ተ/ሚኒስትር አሌሳንድሮ ሎሳና ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ በቅኝ ብትገዛ ብዙ ጥቅም እንደምታገኝና ኢትዮጵያም የምትድነው በኢጣሊያ ስትገዛ ነው ብለው እንደሚያምኑ የተናገሩ ሲሆን ራፋኤሌ ጓርኢግሊያ የተባሉ ሌላ ከፍተኛ የኢጣሊያ ባለ-ስልጣን ደግሞ አፈወርቅን ኢጣሊያ እንዳልገዛቻቸውና አፈወርቅ እራሳቸው የሚከተለውን ሚስጥር እንዳካፈሉት ተናግሯል፣
"ባደረግኩት ሁሉ ሳትገረምና ለኔ ያለህን ክብርም እንዳጣህ አምናለሁ። ነገር ግን ያመንኩበትን አድርጌያለሁ። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በቅኝ ብትይዛትና እያስለጠነች ብታበለጽጋት፣አሜሪካኖች እንግሊዞችን እንዳባረሩት ሁሉ የሰለጠኑና የበለጸጉ ኢትዮጵያውያን ጣሊያንን ከኢትዮጵያ የሚያባርሩበት ቀን እንደሚመጣ አምናለሁ።"
ሆኖም በ1928 ዓ/ም የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት ሲጀመር አፈወርቅ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ።ይህንንም አንዳንድ የነጋድራስ አፈወርቅ ደጋፊዎች የአርበኝነታቸው ማረጋገጫ እንደሆነ አድርገው አቅርበውታል።

ጣሊያኖች አዲስ አበባን እንደተቆጣጠሩ ግን ነጋድራስ አፈወርቅ ያለምንም መሸፋፈን የኢትዮጵያን በኢጣሊያ ቅኝ መገዛት በአደባባይ መደገፍ ጀመሩ።በስደት ወደ ውጭ የሄዱትን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንና በዱር በገደሉ ፋሽስት ኢጣሊያን ሲዋጉ የነበሩትን የኢትዮጵያ አርበኞችንም መርዘኛ በሆኑ ቃላት ማንኳሰስ ጀመሩ።

በሚገርም ሁኔታ ግን አፈወርቅ ለኢጣሊያ ያላቸው ፍቅር እራሳቸውንም ለጊዜው ከፋሽስት በትር ሳያስጥላቸው ቀርቷል። በየካቲት ወር 1929 ዓ/ም የፋሺስት ኢጣሊያ የኢትዮጵያ ገዢ የነበረውን ሩዶልፎ ግራዚያኒን ለመግደል በአብረሃ ደቦጭና በሞገስ አስገዶም

መሪነት በአዲስ አበባ የተደረገውን ሙከራ ተከትሎ አፈወርቅም ተይዘው ወደ ኢጣሊያ እንዲሄዱ ተደረገ።ከ1 አመት በኋላ ግን ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው አፈ-ቄሳር በሚል ማእረግ ፋሽስት ኢጣሊያን በፕሮፓጋንዳ ሹምነት አገልግለዋል።

በ1933 ዓ/ም የፋሽስት ኢጣሊያ ጦር ተሸንፎ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አገር እንደተመለሱ ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ በአገር ክህደት ተከሰው የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው።ይሁን እንጂ የሞት ፍርዱ ወደ እድሜ ልክ እስራት እንዲቀልላቸው ተደርጎ ነጋድረስ አፈወርቅ በደቡብ ምእራብዋ የንግድ ከተማ በጅማ የእስራት ጊዜያቸውን በመፈጸም ላይ ሳሉ አይናቸው ታውሮ በመስከረም ወር 1940 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል። ነፍስ ይማር!

የተያያዘው ምስል የነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ-ኢየሱስ ሲሆን ምስሉ በኢጣሊያ የኢትዮጵያ ጉዳይ ፈጻሚ በነበሩበት ወቅት በ1926/1927 ዓ.ም እንደተነሳ ይታመናል። ምስሉ የተገኘው ከቴል አቪቭ ዩኒቨርስቲ ማእከላዊ ላይብረሪ ነው። የነጋድራስን ተጨማሪ ምስል በአስተያየት መስጫው ላይ መመልከት ይቻላል።
https://en-centlib.ac.il/special-collection-faitlovich
Text Credit: Pioneers of Change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of the Early 20th Century/Prof Bahru Zewde/Ohio University Press/PP 52-58, 108-109"



**ግራዝማች ጸጋይ ሓጎስ ብርቱዕ ዕሊ ምዝካርን ታሪከኛን ኣቦ**

**ምሥጋና፣ንኩልኹም ሓበሬታን ኣሳእልን ዝመጠኩምኒ እብል።ብፍላይ ግን**

- ሰድራ ብላታ (ኣቦይ) ኣጽብሃ ምስ በዓልቲ ቤቶም ማማ ሕይወት፣
- ኣቦይ ጸጋይ ሓጎስ (ግራዝማች ወድ 110 ዓመት ክነሶም ዘይሕለሉ ኣቦ)፣
- ንጸሓፊ ታሪኽ ሲሳይ ተፈራ፣
- ንጸሓፍን ተመራማርን መምህር ኣሰፋው ደገፋው፣
- ንነፍስሔር ዶ/ር ዘውደ ገብረሥላሴን ቤተሰቦምን፣
- ንፕሮፌሰር ኣበባው፣ንፕሮፌሰር ባህሩ ዘውደ፣
- ንቤተሰብ ነጋድራስ ገብረሕይትት ባይከዳኝ፣
- ንጋዜጠኛ የሃና ሃይሉ፣ ኣብ'ዚ ዘይተጠቐስኩምን እብል።



**ፍሉይ ክብሪ፣ንሰናዲ ታሪኽ ኣቦና ኣጽብሃን በዓልቲ ቤቶምን ማማ ሕይወት ይኹነለይ እብል።**